# በኢፌዲሪ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር

## የ2014 በጀት ዓመት የ6 ወራት
## የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት

ጥር/2014 ዓ.ም

<u>አዲስ አበባ</u>

# ማውጫ

መግቢያ ........ 3

1) የመፈጸምና የማስፈጸም አቅምን ማጎልበት፡- (የትኩረት መስክ አንድ) ........ 4

2) የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ማስፋፋት (የትኩረት መሰክ አራት) ........ 11

3) የጥናትና ምርም አቅምን ማጎልበት ........ 14

4) በአፈፃፀም ሂደት ያጋጠሙ ተግዳሮቶች እና የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች ........ 16

አባሪ፡- የዋና ዋና ግቦች አፈፃፀም በትኩረት መስክ ........ 19

## መግቢያ

ዘርፉ ለሀገሪቱ እድገትና ልማት የሚያበረክተውን ወሳኝ አስተዋጽኦና ከሁሉም የኢኮኖሚና ማህበራዊ ዘርፎች ጋር ያለውን ቁርኝት ከግምት ውስጥ በማስገባት ልዩ ትኩረት ከተሰጣቸው ዘርፎች መካከል አንዱ እንደመሆኑ መጠን በአገር አቀፍ ደረጃ በሚዘጋጁ ፕሮግራሞችና ዕቅዶች ውስጥ ከዘርፉ አንጻር የሚቀመጡ ዓላማዎችና ግቦችን መሠረት ያደረገ ስትራቴጂያዊና ዓመታዊ ዕቅዶች በየደረጃዉ በማዘጋጀትና ተግባራዊ በማድረግ ሀገራችን እስከ አሁን ላስመዘገበችዉ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት የበኩሉን አዎንታዊ ሚና አበርክቷል::

በዚሁ መሰረት ሚኒስትር መስሪያ ቤቱ በ2014 በጀት ዓመት የዝግጅት ምዕራፍ የዘርፉን የውጤት ተኮር ዕቅድ ከባለድርሻ አካላት እና ከተጠሪ ተቋማት ጋር በጋራ በማቀድ፣በጋራ መድረክ ዕቅዱን በማዳበር ዕቅዱ በየደረጃው ባለው እርከን እንዲወርድ ተደርጓል፡፡

በዕቅዱ ላይ በተቀመጠው የድጋፍና ክትትል እና የግንኙነት አግባብ መሰረት የበጀት ዓመቱ የ6 ወራት የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት እንደሚከተለው ተዘጋጅቶ ቀርቧል፡፡

### በዝግጅት ምዕራፍ የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት

- በበጀት ዓመቱ የዝግጅት ምዕራፍ የዘርፉን የአስር ዓመት መሪ የልማት ዕቅድ (2013-2022) መሠረት በማድረግ የ2013 በጀት ዓመት ውጤት ተኮር ዕቅድ ተዘጋጅቷል፤
- ከሚኒስቴር መ/ቤቱ፣ ከተጠሪ ተቋማት እና ከክልል ቢሮዎች የተውጣጡ ተሳታፊዎች በጋራ በ2013 በጀት ዓመት የዕቅድ አፈጻጸም እና የ2014 በጀት ዓመት ዕቅድ ላይ መግባባት ላይ በመድረስ እና ቀጣይ አቅጣጫዎች ላይ ስምምነት በመፍጠር ውጤት ተኮር ዕቅዱ በየደረጃው እስከ ፈፃሚ እንዲወርድ ተደርጓል፡፡
- በተዘጋጀዉ የውጤት ተኮር ዕቅድ ላይ በየደረጃው በተደረሰው መግባባት አመራሩና ፈፃሚው የባለቤትነት ስሜት ይዞ ወደ ስራ እንዲገባ ተደርጓል፡፡

1) **የመፈጸምና የማስፈጸም አቅምን ማጎልበት፡-** (የትኩረት መስክ አንድ)

**ግብ 1. የአመራሩን እና የፈፃሚውን እውቀትና ክህሎት ማሳደግና የአመለካከት ለውጥ ማምጣት**

**የአቅም ግንባታ ስልጠናዎች**

- የስልጠና ፍላጎት በዳሰሳ ጥናት ተለይቷል፡፡
- በሚኒስቴር መ/ቤቱ ለ385 ባለሙያዎች የተለያዩ የአጫጭር ጊዜ ስልጠናዎች ለመስጠት ታቅዶ ለ275 (71.4%) ስልጠና ተሰጥቷል::
- በጨርቃጨርቅና አልባሳት ፋብሪካዎች ውስጥ የሚሰሩ ባለሙያዎች ለዩኒቨርስቲ ተማሪዎች እና ለተለያዩ ድጋፍ ሰጪ ተቋማት ላይ ለተሰማሩ ለ640 ባለሙያዎች ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ ለ550 (349 ወንድና 201 ሴት) ሰልጣኞች በተለያዩ የስልጠና ርዕሶች ክፍተትን መሠረት ያደረገ የአቅም ግንባታ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡
- በቆዳ ዘርፍ ያለዉን የሰዉ ኃይል ጥራቱን ከመጠበቅና ምርታማነቱን ከማሳደግ አንፃር የሙያ ብቃት ምዘና ጉልህ ሚና ያለዉ በመሆኑ የባለሙያዎችን የሙያ ብቃት መመዘንና ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ በዚሁ መሰረት ከሙያ ብቃት ምዘናና ማረጋገጫ ማዕከላት የተላኩ 4 ወንድና 1 ሴት በድምር 5 ባለሙያዎች በቆዳ አመራረት በደረጃ ሦስትና አራት የሙያ ብቃት ምዘናን ተመዝነዉ (5)100%/ ብቁ ሆነዋል፡፡እንዲሁም የኢንስቲትዩታችን የቆዳ እቃዎች አመራረት 3 ወንድና 3 ሴት በድምሩ 6 ባለሙያዎች እንዲሁም **የቆዳ እቃዎች አመራረት** ከ16 ተመዛኞች ውስጥ 3 ወንድና 7 ሴት በድምሩ 10 ሰልጣኞችን በደረጃ ሁለት የሙያ ብቃት ምዘናን ተመዝነዉ ብቁ ሆነዋል፡፡

- በብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ ንዑስ ዘርፍ ለተሰማሩት ተቋማት በ10 የስልጠና ዓይነት (ካቲያ ዲዛይን ሶፍትዌር፣ በሶሊድ ወርክ ዲዛይን ሶፍትዊር፣ ሚግ/ቲግ ወልድንግ፣ ሲኤንሲ፣ ኢንዱስትሪያል ሴፍቲ፣ ፕሮጀክት መኔጅመንት፣ ወርክ ኢትክስ፣ ኳልት ማኔጅመንት እና ካይዘን) ወንድ 255፣ ሴት 13 ድምር 268 ስልጠና ተሰጥቷል፡፡ በSave the Children ኘሮግራም በብየዳና ሲኤንሲ ማሽን፣ በኤሌክትሪካልና ኤሌክትሮኒክስ፣ በአውቶሞቲቭና በአልሙኒየም ወ 27 ሴ 6 በጠቅላላው 33 የኢንዱስትሪ ባለሙያዎች ስልጠና ተሰጥቷል፡፡ በአጠቃላይ ወ 282 ሴ 19 በድምሩ 301 የተግባር ስልጠና ተሰጥቷል፡፡ እንዲሁም ለኢንዱስትሪ እና ለቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ኤጀንሲ አመራሮች በፕሮጀክት ማነጅመንት፣በጥራት ማኔጅመንት፣ በጊዜ አመራር እና በሶሊድ ወርክ ዲዛይን ሶፍት ዊር ወንድ 104 ሴት 5 ድምር 109 ስልጠና ተሰጥቷል፡፡
- በምግብ፣ መጠጥና ፋርማሲዩቲካል ለ139 ባለመያዎች የተለያዩ (በጥናትና ምርምር አሰራር፣ መሰረታዊ የአመራረት ትግበራ ስርዓት፣ Tranformatinal Ledership፣ Food Processing፣ Project, Planinig, Montering and Evaluation፣ Business Plan Preparation፣ Grean economiy) የአጫጭር ጊዜ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡
- በኬሚካልና ኮንስትራክሽን ንዑስ ዘርፍ ለሳሙና አምራች ኢንዱስትሪዎች እና ለሳሙና ተመራማሪዎች በAromatic and medicinal plants extraction Methods of Essential oil and Other Crude Extracts with their Application እና training methodology በተሰጠ ስልጠና 52 ሰልጣኞች ከአምራች ኢንዱስትዎች ተሳታፊ ሆነዋል፤የቴክኖሎጂ ሽግግር እና የኢንተርፕነር አስተዳደር እንዲሁም የስራ እድል ፈጠራ ክህሎት ለ65 ሰልጣኞች ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

**የተቋሙ አደረጃጀት እና የሪፎርም ስራዎች አፈፃፀም**

- የተቋሙን አደረጃጀትና የሰው ሃብት ድልድል በሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ፀድቋል:: የሠረተኞች ምድባ ለማካሄድ የድልድል ኮሚቴ ተዋቅሯል፡፡ የተጠሪ ተቋማት ደንብ እና የውስጥ አደረጃጀት ተዘጋጅቷል፡፡
- አገልግሎት አሰጣጥና አሰራርን ቀልጣፋና የተሻለ ከማድረግ አኳያ የኢንደስትሪ መረጃ ስርዓት ለምቶ ተጠናቋል፡፡ መረጃ የማስገባት ስራ እየተሰራ ይገኛል፡፡
- በሚ/ር መ/ቤቱ ሲሰሩ የነበሩና በአዲሱ አደረጃጀት ወደ ሌላ ተቋም የተዘዋወሩ ስራዎች ለሚመለከታቸው ማስረከብ ስራው ተሰርቶ ተጠናቋል ርክክብ ይቀራል፡፡

**የግብዓት አቅርቦት**

**ሰብዓዊ ግብዓት (የሰው ኃይል ማሟላት)**

**የሰው ኃይል**

- ለውሳኔ የሚረዳ የሠራተኞች መረጃ በፆታና በትምህርት ደረጃ ወቅታዊ ተደርጓል፡፡
- የሰው ሀይል ለማሟት በተያዘው ዕቅድ መሠረት በክፍት የሥራ መደቦች ላይ ለውስጥ ሠራተኞች የደረጃ ዕድገት ማስታወቂያ በማውጣት ለ29 (ወንድ= 15 እና ሴት= 14) የውስጥ ሠራተኞች በደረጃ ዕድገት እንዲሟላ ተደርጓል፡፡ እንዲሁም ለ2 ተላለኪ፣ ለ3 ጽዳት ሠራተኛ በድምሩ የአምስት ሴት ሠራተኞች ቅጥር ተከናውኗል፡፡

**ቁሳዊ ግብዓት**

- ለሥራ አስፈላጊ የሆኑ የቢሮ ዕቃዎችን ለማሟላት ጥረት ተደርጓል፡፡
- የመ/ቤቱ ተሽከርካሪዎች ዓመታዊ የኢንሹራንስ ሽፋን እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡
- ለ2793 (87%) ተገልጋዮች የትራንስፖርት ስምሪት አገልግሎት ተሰጥቷል፡፡

**ግብ 2. የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አጠቃቀም ማሳደግ**

- ዓለም አቀፍ፣ አኅጉራዊና ሀገራዊ የቨርቸዋል ሰብሰባዎች እንዲካሄዱ ምቹ ሁኔታዎችን ተፈጥሯል፣
- ኮቪድ-19ን ከመከላከል አንጻር በክፍት የስራ ቦታ ማስታወቂያ በኢሜል እንዲያመክቱ በማድረግ አካላዊ ንክኪ ከግማሽ በላይ እንዲቀንስ ተደርጓል፤ በተጨማሪም ስብሰባዎች በኦንላይን ማካሄድ የሚያስችል ፕላት ፍርም በመግዛት ሚኒስቴር መ/ቤታችን፣ ክልሎችና ተጠሪ ተቋማት እንዲጠቀሙበት ተደርጓል፣
- 18 ሲሲቲቪ ካሜራ እና የዲጂታል የፊርማ መቆጣጠሪያ በመግጠም አላስፈላጊ እንቅስቃዎችን ለመከታተል ተችሏል፣

**ግብ 3. ምቹ የሥራ አካባቢ በመፍጠር የፈፃሚዎችን ውጤታማነት ማሳደግ፡-**

- ለሥራ አስፈላጊ የሆኑ የቢሮ ዕቃዎችን የማሟላት ስራ ተከናውኗል፡፡
- ምቹ ቢሮና የስራ አካባቢ የመፍጠር ስራ እየተሰራ ነው፡፡ በተለይ የካፍቴርያ እና የሚኒስቴር መ/ቤቱ ሰራተኞች የተለያዩ ሸቀጦች በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲገበያዩ የሸማቾች ማህበር ተቋቁሞ አገልግሎት በመስጠት ላይ ነው፡፡
- የቡድን ስራ ስሜት በመፍጠር ለስራ ምቹ ሁኔታ እንዲፈጠር ጥረት ተደርጓል፡፡
- የህፃናት ማቆያ ማዕከል የሚያስፈልጉ ግብአት እና የሰው ኃይል በማሟላት አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል፡፡

**ግብ 4. የሙስና መከላከል ስርዓትን ማሳደግና የመልካም አስተዳደር ሥራዎች አፈፃፀም**

- የሙስናና ብልሹ አሰራርን በጋራ ለመከላከልና ሰራተኞች ጥቆማ የማቅረብ ባህላቸውን ለማሳደግ የጥቆማ መቀበያ ሶፍት ዌር የማበልጸግ የተለያዩ የጥቆማ ማቅረቢያ መንገዶችን

ማለትም ሳጥኖችን በየኮሊደሮች የማስቀመጥና በሳምንት ሁለት ጊዜ የመፈተሽ፣ የኢሜል አድራሻ ከፍቶ ለሰራተኞ የማስተዋወቅና በአካል ተገኝተው መጠቆም እንዲችሉ ሁኔታዎችን የማመቻቸት ስራ ተሰርቷል፡፡

- ከተቋሙ በዝውውር፣በጡረታ እና አገልግሎት ለሚያቋርጡ ሀብት አስመዝጋቢ ሰራተኞች የክሊራንስ አገልግሎት የመስጠት ስራ ተከናውኗል፡፡
- በኦዲት እርምጃ እንዲወሰድባቸው ወይም እንዲስተካከሉ ሪፖርት በቀረበባቸው ጉዳዮች ላይ ችግሮቹ መፈታታቸውን በተቀመጠው የጊዜ ገደብ የማስተካከያ እርምጃ መወሰዱን ክትትል እየተደረገ ይገኛል፡፡
- ሙስናንና ብልሹ አሰራርን በመከላከል ዙሪያ የተሻለ ልምድ ካላቸው የፌደራል መ/ቤት የልምድ ልውውጥ ተደርጓል፡፡
- በተቋሙ አዲስ የስራ ቅጥር ለፈጸሙ ሰራተኞች የሀብት ማሳወቅና ምዝገባ እንዲያከናውኑ ተደርጓል፡፡
- የስራ መሪዎችና ሠራተኞች የሥነምግባር መመሪያ ተዘጋጅቷል፡፡
- በየኢንዱስትሪው የተነሱ እና ክትትልና ድጋፍ የተደረገላቸው እንደ ማስፋፊያ ፕሮጀክት የመሬት ጥያቄዎች ፣የሁለተኛ መደብ ሀ ታሪፍ ተጠቃሚነት ጥያቄዎች ፣የውጭ ሀገር ባለሙያ ፈቃድ እና የመሬት አቅርቦት፣ የኤሌክትሪክ አቅርቦት መቆራረጥና መዋዠቅ ችግሮችን በክትትል እና ድጋፍ መፍታት ተችሏል፡፡ ሆኖም ከውጭ ምንዛሬ ፣ከብድር አቅርቦትና መሰል ጉዳዮች አንጻር የሚነሱ ቀሪ ችግሮችን በፋብሪካ ደረጃ በመለየት ለመፍታት እየተሰራ ይገኛል፡፡

**ግብ 5. የዘርፉን ሥራዎች የሚያሳኩ የጥናት ስራዎችን ማካሄድ**

**የኢንዱስትሪ ፖሊሲ ክለሳ በተመለከተ፤**

- የኢንዱስትሪ ፖሊሲን ለመከለስ በተያዘው ዕቅድ መሠረት የፖሊሲ ክለሳ ጥናቱን 95% ደርሷል፡፡

**በልማት አጋሮች የሚደረጉ ድጋፎች በአንድ ማዕከል አሰባስቦ የመምራት**

- በተቀናጀ መልኩ ከዕቅድ ጋር በማስተሳሰር መምራትና መተግበር ይቻል ዘንድ የተዘጋጀው የልማት አጋር ድርጅቶች ድጋፍ አጠቃቀም እና አስተዳደር ሥርዓት ጥናት 70% ተከናውኗል፡፡

**ግብ 6. የሴቶችን ተጠቃሚነት ማሳደግ**

- ክትትልና ድጋፍ የሚደረግላቸዉን ኩባንያዎች ከሁሉም ከማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ከተጠሪ ተቋማት የሴቶች ጉዳይ የስራ ክፍሎች ጋር በመተባበር 39 ኙን የመለየት ስራ ተሰርቷል፣
- በ2013 በጀት ዓመት የሥርዓተ-ፆታ ጉዳይ አካቶ ለመሥራት ፈቃደኛ የሆኑ ፋብሪካዎች/ ኩባንያዎች ለመደገፍ በታቀደው መሠረት በኦሮሚያ፣ በአዲስ አበባ መስተዳደር ከሚገኙ ፋብሪካዎች/ኩባንያዎች ለሠራተኞች በተለይም ለሴቶች ምቹ የስራ አካባቢን ከመፍጠርና

ተሳታፊና ተጠቃሚ ከማድረግ አኳያ በተሰራው የዳሰሳ ጥናት በተገኘው ውጤት መሰረት በጨርቃጨርቅ ዘርፍ ለተሰማሩ ፋብሪካዎች/ኩባንያዎች ከ UNIDO ጋር በመተባበር ለሁለት ቀን ለ28 ሴት ለ12 ወንድ በድምሩ ለ 40 ተሳታፊዎች በፆታ ጥቃት እና በሥርዓተ-ፆታ ጽንሰ ሀሳብ ዙሪያ የሁለት ቀን የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ተሰጥቷል፤

- የሴቶችን የአመራርና የውሳኔ ሰጪነትን ሚና ለማጎልበት በGIZ ድጋፍ በተዘጋጀ የአቅም ማጎልበቻ አጭር ጊዜ የ3 ወር የገፅ ለገፅ ስልጠና ከተቋሙ 11 ከጨርቃ ጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት 4 በድምሩ 15 በከፍተኛ ኤክስፐርት፣ በቡድን መሪና በዳይሬክተር ደረጃ የሚገኙ ሴቶች አጠናቀው ተመርቀዋል፡፡ ሂደቱን ክትትል የማድረግና የመገደፍ ስራ ተሰርቷል፡፡
- በ2013 በጀት ዓመት ሴቶች በአመራርና ውሳኔ ሰጪነት የሥራ መደቦች በዳይሬክተር ደረጃ ከነበረው 11 ነባራዊ መነሻ ወደ 12 እንዲሁም በቡድን መሪ ደረጃ ከነበረው 25 ነባራዊ መነሻ ወደ 26 ከፍ ብሏል፡፡

**ግብ 7. ቅንጅታዊ አሰራርን ማጠናከር**

- የቆዳ ፋብሪካዎች እያጋጠማቸዉ ያለዉን የደረቅ ቆሻሻ ማወገጃ ቦታ ችግር እና ሌሎችንም ተያያዥ ችግሮች ከባለድርሻ አካላት ጋር የአካባቢ፤ደንና አየር ንብረት ለዉጥ ኮሚሽን፤ ከአ.አ.፤ ከአማራ፤ ከኦሮሚያና ሞጆ አካባቢ ጥበቃ፤ከአ.አ.ጽዳት አስተዳደር ኤጀንሲ እንዲሁም ከተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ጋር ተቀናጅቶ በመስራት፣ስራዎችን በመከታተልና በመገምገም፤ የሚከሰቱ ችግሮችን በጋራ ተወያይቶ መፍትሄ እንዲያገኙ እየተሰራ ነው፡፡
- በምግብ መጠጥና ፋርማሲዩቲካል ዘርፍ የተሰማሩ ከአምራች የኢንዱስትሪ -ዩኒቨርስቱ ትስስር በክላስተር ደረጃ መድረክ ተዘጋጅቷል፡፡ በዚህም
  - 5 ዩኒቨርሲትዎች (ባህርዳር፤ጎንደር፤በአ/አ ሳይንስና ቴክኖሎጂ  እና አርሲ)
  - 4 ቴክኒክና ሙያ ኮሌጆች (ኮልፌ፤ንፋስ ስልክ ፤አቃቂ ፖሊ ቴክኒክ፣ የካ)
  - 5 አምራች ማህበራት እና ከ15 ኢንዱስትሪዎች በመድረኩ ተሳትፈዋል፤
- ዩኒቨርስቲ ኢንዱስትሪ ትስስር፡- የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ የ2ኛና 3ኛ ዓመት የቴክስታይልና የጋርመንት ተማሪዎች በኢንስቲትዩቱ በምርምርና ፍተሻ ዳይሬክቶሬት፤ ይርጋለም ጨ/ፋብሪካና በMNS ጨ/ፋብሪካ በእያንዳንዱ የአንድ ቀን ስልጠና እንዲያገኙ ድጋፍ የተደረገ ሲሆን ከዚሁ ዩኒቨርሲቲ 2 የ5ኛ ዓመት የጨርቃጨርቅ ኢንጂነሪንግ ተማሪዎች በምርምርና ፍተሻ ዳይሬክቶሬት የመመረቂያ የምርምር ስራቸውን እንዲሰሩ ድጋፍ ተደርጎላቸዋል፡፡ ቀደም ሲል ትስስር ተደርጎ ወደ ስራ ለገቡት 4 ነባር (ድሬዳዋ፤ ሀዋሳ፤ አዳማና ወልቂጤ) ትስስር

ንኡስ ቀጠናዎች የ2014 ዓ/ም የዩኒቨርሲቲ-ኢንዱስትሪ ትስስር መነሻ ዕቅድ ተዘጋጅቶ ተልኳል፡፡

- በኬሚካልና ኮንስትራክሽን ንዑስ ዘርፍ ከቴክኒክና ሙያ ተቋማት እንዲሁም ከከተማ መስተዳድር እና ከተለያዩ ሚኒስቴር መስርያ ቤቶች ጋር በእቅድ በተያዘው መሰረት በኢንዱስትሪዎች የሚነሱ ችግሮችን ለመፍታት ቅንጅታዊ መድረኮች ተግባራዊ እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡
- በብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ ኢንዱስትሪ የእሴት ሰንሰለት ውስጥ በየደረጃው ከሚገኙ ባለድርሻ አካላትና ሌሎች ተዋንያንበጋር ለመስራት ስምምነት ላይ ተደሷል፡፡ በዩኒቨርሲቲ ኢንደስትሪ /ቴ/ሙ/ት/ስ/ተቋማት ቅንጅታዊ የትስስር ፎረም በኢንተርን ሺፕ የሰው ኃይል አቅም ለመገንባት ከአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጅ ዩኒቭረስቲ 350፣ ከድሬደዋ ዩኒቨርስቲ 370 እና ከሀዋሳ ዩኒቨርስቲ 378 በተለያዩ ኢንዱስትሪዎች ላይ እንዲሰለጥኑ ተደርጓል፡፡

**ግብ 8. የሀብት/በጀት አጠቃቀምን ማሻሻል**

**የበጀት አፈፃፀም**

በ6 ወራት ውስጥ 357.408 ሚሊዮን ብር ስራ ላይ የዋለ ሲሆን በ2014 በጀት ዓመት የተመደበው የፕሮግራም በጀት ከንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር ጋር ክፍፍሉ ባለመጠናቀቁ ምክንያት ከዕቅዱ ጋር በማነፃፀር ማቅረብ ያልተቻለ ሲሆን በቀጣይ ዝርዝር የበጀት አፈፃፀም የምናቀርብ ይሆናል፡፡

- የ2014 በጀት ዓመት የግዥ ዕቅድ ተዘጋጅቷል፡፡
- የ2014 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ሩብ ዓመት የፋይናንስ ሪፖርት ተጠናቋል፡፡

**የኦዲት አፈፃፀም**

- የ2013 በጀት ዓመት የ4ኛ ሩብ ዓመት የፋይናንስ እና ግዥ ላይ የኦዲት ስራ ተከናውኖ ሪፖርት ቀርቧል፡፡
- የ2013 በጀት ዓመት የ1ኛ እና 2ኛ ሩብ ዓመት የውስጥ ኦዲት የፋይናንስ እና ግዥ ፣ ንብረትና ጠቅላላ አገልግሎት ግኝቶች በተገኙት ግኝቶች ላይ የተወሰደ የማስተካከያና የእርምት እርምጃ የክትትል ኦዲት ስራ ተሰርቶ ከ4ተኛ ሩብ ዓመት የኦዲት ውጤት ጋር ሪፖርት ቀርቧል፡፡
- የየወሩ የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ ስራ ተከናውኗል፡፡
- የበጀት ዓመቱ የ1ኛ ሩብ ዓመት የኦዲት ሥራ በመከናወን ላይ ይገኛል፡፡

**9 መረጃ በመሰብሰብ፣ በማደራጀትና በመተንተን፣ ተደራሽነት ማሳደግ**

- ከውስጥ የስራ ክፍሎች፣ ከክልልና ከከተማ አስተዳደሮች፣ ከባለድርሻ አካላትና ከተጠሪ ተቋማት የተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችን በመጠቀም የዕቅዱን 100% ለመሰብሰብ ተችሏል፡፡
- ለመረጃ ተጠቃሚዎች የተሰራጩ መረጃዎችን በሚመለከት በ6 ወራት ውስጥ 300 ለመስጠት ታቅዶ አፈፃፀሙ 289 (96%) ሆኗል፡፡
- የንግድ፣ ኢንዱስትሪና ገበያ ስታቲስቲክስ ዝግጅት ግብዓት የሚሆን የንግድ፣ ኢንዱስትሪና የገበያ መረጃ አይነቶችና ምንጮች ለመለየት ተችሏል፡፡
- የተለዩትን የንግድ፣ኢንዱስትሪና የገበያ መረጃ አይነቶችን ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች (ተቋማት) መረጃ የመሰብሰብና የማደራጀት ስራ ተሰርቷል፡፡

**2) የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ማስፋፋት (የትኩረት መስክ አራት)**
**ግብ 1:- የማምረት አቅም አጠቃቀም ማሳደግ**

የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ አማካይ የማምረት አቅም አጠቃቀም 50% ለማድረስ ታቅዶ አፈፃፀሙ 46.18% ሆኗል፡፡ የኢንደስትሪዎች የማምረት አቅም አጠቃቀም (capacity utilization) ለማሳደግ የተያዘው ኢላማ ከመነሻ አመቱ ከነበረው 46 በመቶ ወደ 46.18 በመቶ ማሳደግ ተችሏል፡፡ ይህም በ6 ወራት የነበሩ የተለያዩ ተግዳሮቶች ማለትም ኢንደስትሪ የሚያስፈልግ ግብዓት፣ የፋይናንስ አቅርቦት ከውጭ ምንዛሬ እና ፀጥታ ችግር አንፃር አብዛኞች ኢንደስትሪዎች ማምረት የማቆም አዝማሚያ ቢኖራቸውም የተለያዩ የቴክኒክ እና የድጋፍ ስራዎች በመስራት ቀድሞ ከነበራቸው እንዳይቀንሱ በመስራት የተገኘ ነው፡፡

የማምረት አቅም አጠቃቀም በየንዑስ ዘርፍ ሲታይ የጨርቃጨርቅና አልባሳት 56% ለማድረስ ታቅዶ አፈፃፀሙ 54%፣ የምግብና መጠጥ 58.2% ለማድረስ ታቅዶ አፈፃፀሙ 41.3%፣ ኬሚካልና ኮንስትራክሽን 65% ለማድረስ ታቅዶ አፈፃፀሙ 54% እና ብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ 20% ለማድረስ ታቅዶ አፈፃፀሙ 17.3% ሆኗል፡፡

**ግብ 2. የወጪ ምንዛሪ ግኝትን ማሳደግ**

በበጀት ዓመቱ ስድስት ወራት ከማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ 265.4 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ገቢ ለማግኘት ታቀዶ 238.267 ሚሊዮን ዶላር (89.8%) ማሳካት ተችሏል፡፡ ይህ አፈፃፀም ከአምናው በጀት ዓመት ተመሳሳይ ወራት ከተገኘው 187.535 ሚሊዮን ዶላር ጋር ሲነፃፀር በ50.732 ሚሊዮን ዶላር (27%) ብልጫ አስመዝግቧል፡፡

**ግብ 3. ስትራቴጂክ ገቢ ምርትን መተካት**

በኬሚካልና ኮንስትራክሽን ንኡስ ዘርፍ 19.31 ቢሊዮን ብር ዋጋ ያላቸው ምርቶችን ለመተካት ታቅዶ 11.9345 ቢሊዮን ብር መተካት ተችሏል፡፡

በመሰረታዊ ብረታብረት፣ተሽከርካሪ እና ኤሌክትሮኒክስ ንዑስ ዘርፍ 24.76 ቢሊዮን ብር ዋጋ ያላቸው ምርቶችን ለመተካት ታቅዶ 20.065 ቢሊዮን ብር መተካት ተችሏል፡፡

ተኪ ምርቶች በተመለከተ (Import Substitution) በመጀመሪያ ግማሽ ዓመት በአጠቃላይ የንዑስ ዘርፉን ለማሳደግ 6.77 ሚሊዮን ጥንድ ታቅዶ 5.12 ሚሊዮን ጥንድ ጫማ የተመረተ ሲሆን አፈፃፀሙ ከዕቅዱ አንፃር 75.63 በመቶ ነው፡፡ በዚህም ተኪ ምርቶችን (Import Substitution)

በማምረት እና ከውጭ የሚገቡ ምርቶች በማስቀረት 30.9 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ለማስቀረት ታቅዶ ከተመረተው ተኪ ምርት 63.87 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ለማስቀረት ተችሏል፡፡
በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ደረጃ 383,111 ጥንድ ጫማ በ2 ኩባንያዎች ተመርቶ ለተማሪዎቸ እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን በጫማ ምርት ጥራት ላይ የመስፈርት ዝግጅትና የቴክኒክና የምክር ድጋፍ ለኩባንያዎች እና ለከተማ መስተዳድሩ ተሰጥቷል፡፡የትምህርት ቤት ጫማና ቦርሳ ፕሮጀክት በሀገር አቀፍ ደረጃ ሀገራዊ ፖሊሲ እንዲሆን ለማድረግ ከፌዴራልና ከክልል ባለድርሻ አካላት ጋር ሀገር አቀፍ ምክክር የተደረገ ሲሆን በፕሮጀክቱ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ላይ ከተደረሰው የጋራ መግባባት በተጨማሪ በተለይ በአሁኑ ወቅት እንደ ሀገር አላስፈላጊ ከሆነ የውጭ ጥገኝነት ለመላቀቅ የምናደረገውን ሁለንተናዊ ጥረት ከማገዝ አኳያ ሲታይ በዘርፉ ከፍተኛ መጠን ያለውን የገቢ ምርት በመተካት፣ ዜጎች በሀገራቸው ምርት እንዲኮሩ እና በሂደትም የዘርፉን የውጭ ምንዛሪ ግኝት አቅም በእጅጉ በማሳደግ ረገድ ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳለው ግንዛቤ ተይዞበታል፡፡

### ግብ 4. የኢንዱስትሪ ግብዓት አቅርቦት ማሳደግ

ቅድሚያ ትኩረት ለተሰጣቸው ንዑስ ዘርፎች የግብዓት አቅርቦት ለማሟላት የተከናወኑ ተግባራት እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

ለጨርቃጨርቅ ኢንደስትሪዎች በጥጥ ከተሸፈነው መሬት 49,728 ቶን የተዳመጠ ጥጥ ለማግኘት ታቅዶ 35 ቶን የተደመጠ ጥጥ እንደሚገኝ የተገኘው መረጃ ያሳያል፡፡

ለቆዳና ቆዳ ውጤት አምራች ኢንደስትሪዎች በቁጥር 10 ሚሊየን ጥሬ ቆዳና ሌጦ አቅርቦት በማመቻቸት በቆዳው ንዑስ ዘርፍ የተያዙ የምርትና ኤክስፖርት ግቦችን ለማሳካት ዕቅድ ተይዞ የበሬ 0.60 ሚሊየን፣ሌጦ 5.493 ሚሊየን በድምሩ 6.093 ሚሊየን (የዕቅዱን 61%) ጥሬ ቆዳና ሌጦ ቀርቦ ለምርት ሥራ ውሏል፡፡ ይህ አፈፃፀም ከCOVID-19 ጋር በተያያዘ የአለም የቆዳ ምርቶች ገበያ መቀዛቀዝ ጋር ተያይዞ በሀገር ውስጥ ያሉ የቆዳ ኢንደስትሪዎች የጥሬ ቆዳ ፍላጎት በመቀነሱ ምክንያት ነው፡፡ ባለፉት ስድስት ወራት ውስጥ 15 ሚ.ኪ.ግ ኬሚካል ለፋብሪካዎች ይቀርባል ተብሎ ዕቅድ የተያዘ ቢሆንም የቀረበው ግን 7.8 ሚ.ኪ.ግ (52%) ብቻ ነው፡፡ቸግሩን ለመፍታት የቦንድድ ዌርሐውስ ኬሚካል አቅራቢዎች የቆዳ ማልፊያና ማለስለሻ ኬሚካል ለቆዳ ፋብሪካዎች እንዲቀርብና በፋብሪካዎች መካከል በውሰት እንዲያገኙ ድጋፍና ክትትል ተደርጓል፡፡ እንዲሁም 4,600 ኩንታል ኖራ ከደርባን ሲሚንቶ ፋብሪካ ለቆዳ ፋብሪካዎች ለማቅረብ ዕቅድ ተይዞ 3,710 ኩንታል (80.65%) ኖራ ለሁም ቆዳ ፋብሪካዎች እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡

ለምግብና መጠጥ ኢንደስትሪዎች 1,909,477 ቶን የተለያዩ ግብዓቶች ለማቅረብ ታቅዶ 1,548,879.93 ቶን በማቅረብ የዕቅዱን 81.1 በመቶ ሆኗል፡፡

በከፍተኛ መጠን ከውጭ የሚገባውን የአርማታ ብረት ምርት በሀገር ውስጥ አምርቶ መተካት እንዲቻል በቁርጥራጭ ብረት መልክ 4000 ቶን በዘርፉ ላሉ 8 ኢንደስትሪዎች ግብዓት የሚሆን ለእያንዳንዳቸው 500 ቶን (ከ165 ሚሊየን ብር) ቁርጥራጭ ብረት ድልድል ተደርጓል፡፡

**ግብ 5. በማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ የተሰማሩ ድርጅቶች የቀረጥ ማበረታቻ ስርዓቶችን ተጠቅመው በአለምና በሀገር ውስጥ ገበያ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ማበረታታት**

- 25 የጨርቃ ጨርቅና ቆዳ ምርቶች ላይ ለሚነሱ የስታንዳርድ የግብአት ምርት ጥምርታ ጥያቄዎች ማስተካከያዎች ለማድረግ ታቅዶ አፈፃፀሙ 14 ሆኗል፡፡
- 12 ድርጅቶች አዲስ የቫውቸር ስርዓት ተጠቃሚነት ሠርተፊኬት ለመስጠት ስርዓቱን ለመጠቀም ጥያቄ ያቀረቡ ድርጅቶች 19 በመሆናቸው ምክንያት ክንውኑ የዕቅዱ 158% ሆኗል፡፡
- ለ46 (93.9%) የቫውቸር ስርዓት ተጠቃሚነት እድሳት የጥያቄያቸውን ትክክለኛነት በማረጋገጥ እና ስ/ግ/ም/ጥመርታ ላልወጣላቸው ዘርፎች ግ/ም/ጥመርታ በማዘጋጀት የሰርተፍኬቶች እድሳት ተደርጎላቸዋል፡፡
- በ60 ኢንዱስትሪዎች መካከል የምርትና ግብዓት ትስስር ኮንትራታዊ ውሎችን እንዲፈፀሙ ለማድረግ ታቅዶ አፈፃፀሙ 101 ሆኗል፡፡
- የቀረጥ ተመላሽ ጥያቄ ያቀረቡ 2 ድርጅቶች የጥያቄያቸውን ትክክለኛነት በማረጋገጥ እና ስ/ግ/ም/ጥመርታ ላልወጣላቸው ዘርፎች ግ/ም/ጥመርታ በማዘጋጀት ጥያቄያቸው ምላሽ አግኝቷል፡፡
- ለ56 የተለያዩ ማስተካከያ (የተጨማሪ ግብዓት፣ የመለኪያ ለውጥ ማስተካከያ፣ የተተካኪ ግብዓት፣ የግብዓት ጥምርታ ለውጥ) ጥያቄዎችን በመመርመር የግብዓት ምርት ጥመርታው እንዲፀድቅላቸው ተደርጓል፡፡
- ለ8 የጉምሩክ ሁለተኛ ምድብ ሀ ታሪፍ ማበረታቻ ተጠቃሚነት ጥያቄ ትክክለኛነት በማረጋገጥ እና ግብዓት ምርት ጥመርታ በማዘጋጀት ሠርተፊኬት ታድሷል፡፡ እንዲሁም ለ7 አዲስ የሁለተኛ ታሪፍ ምድብ ሀ ማበረታቻ ተጠቃሚዎች ጥያቄ ትክክለኛነት በማረጋገጥ እና ግብዓት ምርት ጥመርታ በማዘጋጀት ሰርቲፍኬት ተሰጥቷል፡፡
- ለ1 ድርጅት የግብዓት መጠቀሚያ/ መሸጫ ጊዜ እንዲራዘምለት ተደርጓል፡፡

**ግብ 6. የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ኢንቨስትመንትን ማሳደግ**

6.1 ወደ ትግበራ (ግንባታ) የገቡ እና ወደ ማምረት የተሸጋገሩ ፕሮጀክቶች በየንዑስ ዘርፉ፡

6.1.1 ምግብ፣መጠጥና ፋርማሲዩቲካል ኢንዱስትሪ

- ወደ ትግበራ (ግንባታ) የገቡ አዳዲስና የማስፋፊያ ኢንዱስትሪዎች ዕቅድ 69፣ ክንዉን 74፣

- ተጠናቀው ወደ ማምረት የተሸጋገሩ ፕሮጀክቶች ዕቅድ 24 ክንዉን 20፣

6.1.2 ብረታብረትና ኢንጂነሪንግ ኢንዱስትሪ ወደ ማምረት የተሸጋገሩ 8 ታቅዶ አፈፃፀም 8 (100%) ፤

6.1.3 ኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓቶች ኢንዱስትሪ ወደ ማምረት የተሸጋገሩ 3 ታቅዶ አፈፃፀም 3 (100%) ፤

6.1.4 ቆዳ ኢንዱስትሪ ወደ ማምረት የተሸጋገሩ 2 ታቅዶ አፈፃፀም 1 (50%) ፤

### 6.2 አዳዲስ አነስተኛ ኢንዱስትሪዎችን ማበራከትና ነባሮችን ማጠናከር

- 1658 አዳዲስ አነስተኛና መካከለኛ ኢንዱስትሪዎችን ለማቋቋም ታቅዶ አፈፃፀሙ 557 (34%) ሆኗል፡፡
- 2,924 አነስተኛና መካከለኛ ኢንዱስትሪዎችን ለማጠናከር ታቅዶ አፈፃፀሙ 6631 ሆኗል፡፡

### ግብ 7. የአረንጓዴ ማኑፋክቸሪንግ ስትራቴጂና ኢነርጂ ኢፊሸንሲ ስትራቴጂ በመተግበር የካርበን ልቀትን መቀነስ

- ለ43 ፋብሪካዎች የአካባቢ ጥበቃ መመዘኛን እንዲያሟሉ ድጋፍ ተደርጓል፡፡
- የአረንጓዴ አሻራ <<ኢትዮጵያን እናልብሳት>> በሚል መርሃ ግብር በ 3 ዙር 12,000 የተለያዩ ችግኞች በቦሌ ለሚና በቅሊንጦ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ ተከላ ተከናውኗል፡፡

### ግብ 8. ከማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ የሚፈጠረው የሥራ ዕድል ማሳደግ፣

በኢንዱስትሪ አዳዲስና ማስፋፊያ ፕሮጀክቶች የኢንቨስትመንት ሂደታቸውን በማፋጠን ለ96.4 ሺህ ዜጎች የሥራ ዕድል ለመፍጠር ታቅዶ ኢንስቲትዩቶች በሚከታተሏቸው እና ወደ ማምረት በተሸጋገሩ ፕሮጀክቶች ለ74.5 ሺህ (77.3%) ዜጎች የሥራ ዕድል ተፈጥሯል፡፡

### 3) የጥናትና ምርምር አቅምን ማጎልበት

በ6 ወራት ችግር ፈቺ ጥናቶች አፈፃፀም በየንዑስ ዘርፍ ሲታይ፡-

- ጨርቃጨርቅ 9 ታቅዶ አፈፃፀም (77.8%) ፤
- ቆዳና የቆዳ ውጤቶች የጫማ ፋብሪካዎች ምርታማነትንና ተወዳዳሪነታቸውን የሚያግዙ አዳዲስ ምርቶች በመስራት የምርት ስብጥራቸውን እንዲያስፋፉ ከማድረግ አኳያ አዳዲስ የጫማ ሞዴሎች ለመስራት የሚረዱ የፓተርን ግሬዲንግ፤የዲዛይን (መዝገብ ብዜት በቁጥር እና ፍጆታ ልኬት) ለአራት ጫማ አምራች ኩባንያዎች በድምሩ 51 ሴሪ የፓተርን ግሬዲንግ ስራ ድጋፍ ተድርጓል፤ ከስድስትት ወራት 100 ስሪ እቅድ አንፃር ሲታይ  አፈፃፀሙ 51 በመቶ መስራት ተችሏል፡፡

- ብረታብረት 4 ታቅዶ አፈፃፀም 4 (100%)፡
- ምግብ፣መጠጥና ፋርማሲዩቲካል 16 ታቅዶ አፈፃፀም 13 (81.2%)፡
- ኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓቶች 3 ታቅዶ አፈፃፀም 3 (100)፡

## 4) በአፈፃፀም ሂደት ያጋጠሙ ተግዳሮቶች እና የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች

### 4.1 ያጋጠሙ ተግዳሮቶች

1. የግብዓት አቅርቦት፣
2. የውጭ ምንዛሬ፣
3. የፋይናንስ አቅርቦት፣
4. የፀጥታ ችግር፣
5. በአገዋ የተገኘው የገበያ እድል መቋረጥ፣
6. የሎጅስቲክስ ችግር፣
7. የቅንጅት ስራዎች በሁሉም ባለድርሻ አካላት ትኩረት አለማኘታቸው፤

### 4.2 የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች

1. የማምረት አቅም ለማሻሻል በተለይም የግብዓት፣ የውጭ ምንዛሬና የፋይናንስ ጋር የተያያዙ ችግሮች ለመፍታት የተመረጡ ኢንደስትሪዎች ላይ የመስክ ምልከታ በማድረግ የቅንጅት ዕቅድ ከባለድርሻ አካላት ጋር ተዘጋጅቷል፡፡
2. የማምረት አቅም አጠቃቀምንና የሚሰጠውን ድጋፍ ወጥነት ባለው መንገድ ለመምራት የሚያስችል ማንዋል እና የስልጠና ቢጋር በመዘጋጀት ላይ ይገኛል፡፡
3. በደሴ፣ ኮምቦልቻ፣ ጭፍራ እና በበርሃሌ አከባቢዎች የተጎዱ ኢንደስትሪዎችን ለመደገፍ የመስክ ምልከታ በማድረግ ከባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት ተደርጎ ችግሮቹን ለመፍታት የሚያስችል መርሃግብር ተዘጋጅቷል፡፡
4. የሀገር ውስጥ እና ሌሎች የገበያ አማራጮችን ለመጠቀም እየተሰራ ነው፡፡ እንዲሁም የሃገር ውስጥ ገበያ እንዲጠቀሙ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን እየተሰራ ነው፡፡

5. የዲያስፖራዎችን መምጣት ተከትሎ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አላት ጋር በመሆን ለተከታታይ 5 ቀናት አምራች ኢንዱስትሪዎች የተሳተፉበት ኤግዚቢሽን እና ባዛር ተዘጋጅቷል፡፡ የፕሮግራሙ ዋና ዓላማ የገበያ ትስስር መፍጠር ሲሆን ዳያስፖራው በሚመለስበት ወቅት ምርቶቹን ገዝቶ ውጭ ላለው የዓለም ህብረተሰብ እንዲያስተዋውቅ ማድረግ ነው፡፡

## አባሪ፡- የዋና ዋና ግቦች አፈፃፀም በትኩረት መስክ

| ተ.ቁ. | ዋና ዋና ግቦች | መለኪያ | የ2014 በጀት ዓመት /የ6 ወራት/ | | | መግለጫ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ዕቅድ | ክንውን | አፈፃፀም በመቶኛ | |
| ሀ | **የመፈጸምና የማስፈጸም አቅምን ማጎልበት (ትኩረት መስክ አንድ)** | | | | | |
| 1 | የአመራሩንና የፈፃሚዎችን ዕውቀት፣ ክህሎትና አመለካከት ማሻሻል | | | | | |
| 1.1 | በሚኒስቴር መ/ቤቱ (የተሰጠ የአቅም ግንባታ ስልጠና)፣ | በቁጥር | 385 | 275 | 71.4 | |
| 1.2 | የጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት | በቁጥር | 640 | 550 | 86 | ለ550 (349 ወንድና 201 ሴት) ሰልጣኞች በተለያዩ የስልጠና ርዕሶች ክፍተትን መሠረት ያደረገ የአቅም ግንባታ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡ |
| | | በቁጥር | 40 | 29 | 73 | የአጫጭር ጊዜ ስልጠና ያገኙ የኢንስቲትዩቱ ባለሙያዎች፤ |
| 1.3 | የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት | በቁጥር | | 5 | | ከሙያ ብቃት ምዘናና ማረጋገጫ ማዕከላት የተላኩ 4 ወንድና 1 ሴት በድምር 5 ባለሙያዎች በቆዳ አመራረት በደረጃ ሦስትና አራት የሙያ ብቃት ምዘናን ተመዝነዉ (5)100%/ ብቁ ሆነዋል፡፡ |
| | | በቁጥር | | 16 | | የኢንስቲትዩቱ 6 ባለሙያዎች እንዲሁም የቆዳ እቃዎች አመራረት ከ16 ተመዛኞች ውስጥ 10 ሰልጣኞችን በደረጃ ሁለት የሙያ ብቃት ምዘናን ተመዝነዉ ብቁ ሆነዋል፡፡ |
| | | በቁጥር | | 10 | | ከ5 ቆዳ ፋብሪካዎች(ሞጆ ቆዳ፤ኢትዮጵያ ቆዳ፤ባቱ፤ኤሊኮ-አዋሽ እና ኤሊኮ-አቢሲንያ) ለተወጣጡ 10 የቆዳ ባለሙያዎች በፒክል እና በታኒንግ ላይ አዲሱ ቴክኖሎጂ ላይ የተግባር ስልጠና ተሰጥቷል፡፡ |
| 1.4 | የብረታ ብረት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት /ለንዑስ ዘርፉ ባለሙያዎች የንድፈ ሃሳብና የተግባር ስልጠና መስጠት/ | የሰለጠኑ ሠልጣኞች ብዛት በቁጥር | 400 | 410 | 102 | |
| | | የተመዘኑ ባለሙያዎች በቁጥር | 85 | 41 | 48 | |
| 1.5 | የምግብ፣ የመጠጥና የፋርማሲዩቲካል ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት | | | | | |
| | የኢንስቲትዩቱ ባለሙያዎች | በቁጥር | 247 | 139 | 56.3 | ለ139 ባለመያዎች የተለያዩ (በጥናትና ምርምር አሰራር፣ መሰረታዊ የአመራረት ትግበራ ስርዓት፣ Tranformatinal Ledership፣ Food Processing፣ Project, Planinig, Montering and Evaluation፣ Business Plan Preparation፣ Grean economiy) የአጫጭር ጊዜ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡ |
| | የኢንዱስትሪ ባለሙያዎች | በቁጥር | 75 | 82 | 109 | |
| 1.6 | የኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓቶች ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት | በቁጥር | 222 | 208 | 94 | |

| ተ.ቁ. | ዋና ዋና ግቦች | መለኪያ | የ2014 በጀት ዓመት /የ6 ወራት/ | | | መግለጫ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ዕቅድ | ክንውን | አፈፃፀም በመቶኛ | |
| 1.7 | የአነስተኛና መካከለኛ ማፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ማስፋፊያ ባከስልጣን /ግንዛቤ የተፈጠረላቸው ህብረተሰብ ክፍሎች/ | በቁጥር | 6916 | 2414 | 35 | |
| **ለ** | **የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ማስፋፋት (ትኩረት መስክ ሁለት)** | | | | | |
| 1 | የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ የማምረት አቅም አጠቃቀም ማሳደግ | | | | | |
| | ኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓቶች ኢንዱስትሪ ንዑስ ዘርፍ | በመቶኛ | 65 | 54 | 83 | |
| | ምግብ፣መጠጥና ፋርማሲዩቲካል | በመቶኛ | 58.2 | 41.3 | 71 | |
| | ብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ ኢንዱስትሪ ንዑስ ዘርፍ | በመቶኛ | 20 | 17.3 | 86.5 | |
| | ጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪ ንዑስ ዘርፍ | በመቶኛ | 56 | 54 | 96.4 | |
| 2 | የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ምርቶች የኤክስፖርት ገቢ ማሳደግ | | | | | |
| | ጨርቃጨርቅና አልባሳት ን.ዘርፍ | በሺ.ህ የአሜሪካን ዶላር | 97,073.18 | 92,042.25 | 94.8 | |
| | ቆዳ ኢንዱስትሪ ን.ዘርፍ | ›› | 35,819.94 | 21,538.53 | 60.1 | |
| | ምግብ፣መጠጥና ፋርማሲዩቲካል | ›› | 52,284.86 | 46,780.78 | 89.5 | |
| | ሥጋና ወተት ን.ዘርፍ | ›› | 47,714.0 | 55,286.61 | 115.9 | |
| | ብረታብረትና ኤሌክትሮኒክስ | ›› | 25,613.00 | 11,489.90 | 78.4 | |
| | ኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓቶች | ›› | 6,898.33 | 11,128.98 | 161 | |
| | **ድምር** | በሺ.ህ የአሜሪካን ዶላር | **265,403.29** | **238,267.05** | **89.8** | ከአምናው በጀት ዓመት ተመሳሳይ ወራት ከተገኘው 187.535 ሚሊዮን ዶላር ጋር ሲነፃፀር በ50.732 ሚሊዮን ዶላር (27%) ብልጫ አስመዝግቧል፡፡ |
| 3 | ስትራተጂክ ገቢ ምርቶችን መተካት | | | | | |
| | ኬሚካልና ኮንስትራክሽን ንኡስ ዘርፍ | በቢሊዮን ብር | 19.31 | 11.93 | 62 | |

| ተ.ቁ. | ዋና ዋና ግቦች | መለኪያ | የ2014 በጀት ዓመት /የ6 ወራት/ | | | መግለጫ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ዕቅድ | ክንውን | አፈፃፀም በመቶኛ | |
| | መሰረታዊ ብረታብረት፣ተሽከርካሪ፣ ኤሌክትሮኒክስ ንዑስ ዘርፍ | በሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር | 132.65 | 112.282 | 84.6 | |
| | ምግብ፣መጠጥና ፋርማሲዩቲካል የሀገር ውስጥ የገበያ ድርሻ ማሳደግ | በመቶኛ | 37 | 44.12 | 119 | • የምግብ ዘይት፣ ፓስታና አልሚ ምግቦች፣ብቅል እና መድሀኒት በሀገር ውስጥ የተመረተ 547,654 ቶን ሲሆን ከዉጭ የገባ 693,552 ቶን ነው። |
| | | በቶን | 941,622 | 547,654 | 58.2 | |
| | የቆዳ ኢንዱስትሪ ንዑስ ዘርፍ | በሚሊዮን ጥንድ | 6.77 | 5.12 | 75.6 | ተኪ ምርቶችን (Import Substitution) በማምረት እና ከውጭ የሚገቡ ምርቶች በማስቀርት30.9 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ለማስቀረት ታቅዶ ከተመረተው ተኪ ምርት 63.87 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ለማስቀረት ተችሏል። |
| | | በጥንድ | | 383,111 | | • በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ደረጃ 383,111 ጥንድ ጫማ በ2 ኩባንያዎች ተመርቶ ለተማሪዎች እንዲቀርብ ተደርጓል። |
| 4 | የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ የግብዓት አቅርቦት ማሳደግ | | | | | |
| | የጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪ የተዳመጠ ጥጥ | በሺ.ህ ቶን | 49.7 | 35 | 70.4 | |
| | የቆዳ ኢንዱስትሪ | ጥሬ ቆዳና ሌጦ (በሚ.ቁ) | 10 | 6.093 | 61 | |
| | | ኬሚካል በሚሊዮን ኪ.ግ. | 15 | 7.8 | 52 | |
| | ምግብ፣መጠጥና ፋርማሲዩቲካል | በቶን | 1,909,477 | 1,548,879.9 | 81 | • 877,217.34 ቶን ከሀገር ውስጥ የቀረበ ግብዓት ነው። |
| | ብረታብረት ኢንዱስትሪ (ቁርጥራጭ ብረት) | በቶን | | 4,000 | | • በዘርፉ ላሉ 8 ኢንደስትሪዎች ግብዓት የሚሆን ለእያንዳንዳቸው 500 ቶን ቁርጥራጭ ብረት ድልድል ተደርጓል። |
| | ኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓቶች (የሀገር ውስጥ ግብዓት ድርሻ) | በመቶኛ | 65 | 52 | 80 | • የገበያ ትስስር በመፍጠር አምራች ኢንዱስትሪው የሀገር ውስጥ ግብአትን ለመጠቀም የሚያስችል ስራ ተሰርቷል። |
| 5 | የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ኢንቨስትመንትን ማሳደግ | | | | | |
| 5.1 | በግንባታ ላይ ያሉ ፕሮጀክቶች ወደ ማምረት እንዲሸጋገሩ ድጋፍና ክትትል ማድረግ | ወደ ማምረት የተሸጋገሩ ፕሮጀክቶች በቁጥር | 37 | 32 | 86.5 | |

| ተ.ቁ. | ዋና ዋና ግቦች | መለኪያ | የ2014 በጀት ዓመት /የ6 ወራት/ | | | መግለጫ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ዕቅድ | ክንውን | አፈፃፀም በመቶኛ | |
| | ምግብ፣መጠጥና ፋርማሲዩቲካል | ›› | 24 | 20 | 83.3 | |
| | ኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓቶች | ›› | 3 | 3 | 100 | |
| | ብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ | ›› | 8 | 8 | 100 | |
| | የቆዳ ኢንዱስትሪ (የጓንት ፕሮጀክቶች) | ›› | 2 | 1 | 50 | |
| 5.2 | አዲስ የተቋቋሙ አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንዱስትሪዎች | በቁጥር | 1658 | 557 | 34 | |
| 5.3 | የተሸጋገሩ ኢንዱስትሪዎች | | | | | |
| | ከአነስተኛ ወደ መካከለኛ | በቁጥር | 113 | 139 | 123 | |
| | ከመካከለኛ ወደ ከፍተኛ | በቁጥር | 5 | 2 | 40 | |
| 6 | በማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ የተሰማሩ ድርጅቶች የቀረጥ ማበረታቻ ስርዓቶችን ተጠቅመው በአለምና በሀገር ውስጥ ገበያ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ማበረታታት | | | | | |
| | ስታንዳርድ የግብአት ምርት ጥምርታ በተዘጋጀላቸው የጨርቃ ጨርቅና ቆዳ ምርቶች ላይ የሚነሱ ጥያቄዎችን በማጣራት ማስተካከያዎች ማድረግ | በቁጥር | 25 | 14 | 56 | |
| | አዲስ የቫውቸር ስርዓት ተጠቃሚነት ጥያቄ ለሚያቀርቡ ባለሀብቶች የጥያቄያቸውን ትክክለኛነት በማረጋገጥ እና ስ/ግ/ም/ጥመርታ ላልወጣላቸው ዘርፎች ግ/ም/ጥመርታ በማዘጋጀት ሰርተፍኬት መስጠት | በቁጥር | 12 | 19 | 158 | |
| | የቫውቸር ስርዓት ተጠቃሚነት እድሳት ጥያቄ ሲቀርብ የጥያቄያቸውን ትክክለኛነት በማረጋገጥ እና ስ/ግ/ም/ጥመርታ ላልወጣላቸው ዘርፎች ግ/ም/ጥመርታ በማዘጋጀት የሰርተፍኬቶች እድሳት ማድረግ | በቁጥር | 49 | 46 | 93.9 | |
| | በኢንዱስትሪዎች መካከል የምርትና ግብዓት ትስስር ኮንትራታዊ ውሎችን እንዲፈፀሙ ማድረግ፣ ግብዓቶቹ ለመፅደቃቸው ማረጋገጥ እና ደብዳቤ ማዘጋጀት | በቁጥር | 60 | 101 | 168 | |
| | የቀረጥ ተመላሽ ተጠቃሚነት ጥያቄ | በቁጥር | 5 | 2 | 40 | |

| ተ.ቁ. | ዋና ዋና ግቦች | መለኪያ | የ2014 በጀት ዓመት /የ6 ወራት/ | | | መግለጫ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ዕቅድ | ክንውን | አፈፃፀም በመቶኛ | |
| | ለሚያቀርቡ ባለሀብቶች የጥያቄያቸውን ትክክለኛነት በማረጋገጥ እና ስ/ግ/ም/ጥመርታ ላልወጣላቸው ዘርፎች ግ/ም/ጥመርታ በማዘጋጀት ማስተናገድ | | | | | |
| | የተለያዩ የማስተካከያ (የተጨማሪ ግብዓት፣ የመለኪያ ለውጥ ማስተካከያ፣ የተተካኪ ግብዓት፣ የግብዓት ምርት ጥመርታ ለውጥ) ጥያቄዎች ትክክለኛነት በማረጋገጥና ግ/ም/ጥመርታ ለሚያስፈልጋቸው በማዘጋጀት ማስተናገድ | በቁጥ | 35 | 56 | 160 | |
| | የግብዓት መጠቀሚያ/ መሸጫ ጊዜ ማራዘሚያ ጥያቄን ማስተናገድ | በቁጥር | 6 | 1 | 16.7 | |
| | አዲስ የሁለተኛ ታሪፍ ምድብ ሀ ማበረታቻ ተጠቃሚዎች ጥያቄ ትክክለኛነት በማረጋገጥ እና ግብዓት ምርት ጥመርታ በማዘጋጀት ሰርተፍኬት መስጠት | በቁጥር | 5 | 7 | 140 | |
| | የጉምሩክ ሁለተኛ ምድብ ሀ ታሪፍ ማበረታቻ ተጠቃሚነት ጥያቄ ትክክለኛነት በማረጋገጥ እና ግብዓት ምርት ጥመርታ በማዘጋጀት ሠርተፊኬት ማደስ | በቁጥር | 17 | 8 | 47 | |
| 7 | ከማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ የሚፈጠረው የሥራ ዕድል ማሳደግ | | | | | |
| | ጨርቃጨርቅና አልባሳት ን.ዘርፍ | በቁጥር | 7,100 | 7,480 | 105 | ከተፈጠረው የሥራ ዕድል ውስጥ 5,663 ሴቶች ናቸው። |
| | ምግብ፣መጠጥና ፋርማሲዩቲካል | ›› | 32,379 | 26,635 | 82.3 | ከተፈጠረው የሥራ ዕድል ውስጥ 7,512 ሴቶች ናቸው። |
| | የቆዳ ኢንዱስትሪ | ›› | 1,770 | 2,675 | 151 | ከተፈጠረው የሥራ ዕድል ውስጥ 1,881 ሴቶች ናቸው። |
| | ብረታብረትና ኤሌክትሮኒክስ | ›› | 4,000 | 3,817 | 95.4 | ከተፈጠረው የሥራ ዕድል ውስጥ 1,309 ሴቶች ናቸው። |
| | ኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓቶች | ›› | 5,730 | 5,371 | 94 | ከተፈጠረው የሥራ ዕድል ውስጥ 2,283 ሴቶች ናቸው። |
| | አነስተኛ እና መካከለኛ | ›› | 45,479 | 28,577 | 62.8 | |
| | ድምር | በቁጥር | 96,458 | 74,555 | 77.3 | |
| 8 | የአረንጓዴ ማኑፋክቸሪንግ ስትራቴጂና ኢነርጂ ኢፊሽንሲ ስትራቴጂ በመተግበር የካርበን ልቀትን መቀነስ | | | | | |
| | የአካባቢ ጥበቃ መመዘኛን | በቁጥር | 46 | 43 | 93.5 | |

| ተ.ቁ. | ዋና ዋና ግቦች | መለኪያ | የ2014 በጀት ዓመት /የ6 ወራት/ | | | መግለጫ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ዕቅድ | ክንውን | አፈፃፀም በመቶኛ | |
| | እንዲያሟሉ ድጋፍ የተደረገላቸው ፋብሪካዎች | | | | | |
| | የችግኝ ተከላ ማካሄድ | በዙር | 3 | 3 | 100 | የአረንጓዴ አሻራ <<ኢትዮጵያን እናልብሳት>> በሚል መርሃ ግብር በ 3 ዙር 12000 የተለያዩ ችግኞች በቦሌ ለሚና በቅሊንጦ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ ተከላ ተከናውኗል፡፡ |
| | ኢንዱስትርዎች የኢነርጂ ኢፊሸንሲ ስራ ተግባራዊ እንድያደርጉ ማድረግ | በቁጥር | 9 | 6 | 66.7 | |
| **ሐ** | **የጥናትና ምርምር አቅምን ማጎልበት (ትኩረት መሰክ ሦስት)** | | | | | |
| | የጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት | በቁጥር | 9 | 7 | 77.8 | |
| | የብረታብረት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት | በቁጥር | 4 | 4 | 100 | |
| | የምግብ፣መጠጥና ፋርማሲዩቲካል ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት | በቁጥር | 16 | 13 | 81.2 | |
| | የኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓቶች ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት | በቁጥር | 3 | 3 | 100 | |